በዓለ እርገት

ከመ/ ቤዛ ዓለሙ
ም ሸዋ ቱሉቦሉ

በርእሱ የተገለጸው በዓለ ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በተነሣ በአርባ ቀኑ ወደ ቀደመክብሩ መመለሱን ወይም ማረጉን የሚገልጽ የመታሰቢያ ዕለት ነው ። ስለሆነም በየዓመቱ በሁሉም የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በታላቅ ሥነ ሥርዓት ይከበራል አከባበሩም በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ ሲሆን በተለይ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት በንግሥ ይከበራል ።

ስለዚህም ትንሣኤ የዋለበትን ዕለት ይዘን አርባ ቀን በመቁጠር በዓሉ የሚውልበትን ማወቅ ይቻላል። ዕለቱም ሐሙስን አይለቅም ። የዘንድሮው በዓለ ዕርገት የሚውለው ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም መሆኑንም ሳንጠቁም አናልፍም ።

ይህ ዕለት ከጌታ ተሰዓቱ /ዘጠኙ/ ዐበይት በዓላት አንዱ ሆኖ እንዲከበር ቤተ ክርስቲያናችን ወስናለች የወሰነችበትንም ምክንያታዊ ሁኔታ በቅዱስ መጽሐፍ የተመዘገበውን ብንመለከት ጥልቅና ረቂቅ ምሥጢር ከማግኘታችንም ሌላ የበዓሉን ክብር በበለጠ ኀውቀን ለማክበር ስለሚያስችለን እንደሚከተለው እንመለከታለን ።

“ዐርገ እግዚአብሔር ብይባቤ /እግዚአብሔር በልዕልታ (በመለከት ድምፅ) ዐረገ /ፀ፮ መዝ ፶፮፡፭ ይላል ልበ አምላክ ዳዊት ስለዚች ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ይህን ትንቢት ለመተንበይ ችሏል ። የቃሉም ምሥጢር ምርምር የሚያሻው ነው ። ይኸውም እግዚአብሔር በዓለም ምሉዕ ሲሆን «ዐረገ» መባሉ ለምንድ ነው? ዐርገስ የተባለው ማነው ? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያስከትል በመሆኑ ትምህርታዊ ነው ። የጥያቄዎቹም መልሶች የሚከተለው ነው ።

ይህ ትንቢታዊ ቃል የተዋህዶን ምሥጢር የሚገልጽ ነው ። ይኸውም እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ከፈጸመ በኋላ በሞቱ ምትን ድል አድርጎ ለሁላችን ተስፋ የሆነውን ትንሣኤውን ለምስክሮቹ ለሐዋርያት ለአርባ ቀናት ያህል ካረጋገጠላቸው በኋላ ውስንና ትሑት የነበረው ሥጋ ምሉዕና ልዑል ሆኖ ነቢረየማን ለመያዝ ወደ ክብሩ መንበር ወጥቶ በአብ ዕሪና ማለትም ከአብ ጋር የሥልጣን እኩልነትን በመያዝ ሥጋ በተዋህዶ የሚገኘውን ክብር ይህ ነቢይ አስቀድሞ ተነበየ እንደገናም ክብሩም ሆነ ስሙ እግዚአብሔርነት መሆኑን ፍጹም ተዋህዶውን መስክሮአል ። የሥጋን እግዚአብሔርነት ለሚጠራጠሩም ጥልቅ ትምህርት ሰጥቶ አልፎአል ።

ይኸው ነቢይ ትንቢቱን በመቀጠል «ዐረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ» /ወደ ላይ ዐረግህ ምርኮን ማረክህ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ / (መዝ ፷፯፡፲፰) በማለት እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዓላማ በአጭር ቃል አስረድቶአል ። ለአምላካችን ክብር ምሲጋና ይገባውና የአዳምን ዘር ከጥንቱ ጠላቱ ሰይጣን ማርኮ ወደ ቀደመ ልጅነቱ መልሶት ሲያርግ ጸጋን (ስጦታን)አጎናጽፎታል ። ጸጋውም ልጅነት ብቻ ሳይሆን ሥልጣንንም ጭምር እንዲሆን ቅዱስ ጳውሎስ እንደዚህ ሲል ገልጾታል ። “ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ . . . እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት ፣ ሌሎችም ነቢያት ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ” (ኤፌ፡፬፡፰-፲፪) ብኋል ከዚህ ኃይል ቃል የምንማረው እንደገና ወደ ምርኮ ተመልሰን ፈቃደ ሥጋችንንና ነፍሳችንን ለአጋንንት ካላስገዛን የሐዋርያትና የነቢያት ወዘተ . . . ጸጋ እንደምንታደል ነው ።

ጌታ በሚያርግበት ጊዜ ዳግመኛ ወደ ምርኮ እንዳይመለሱ ለደቀ መዛ

ሙርቱ የሰጣቸው መመሪያም “እንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም (እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ) በማለት ስንብት ወደሚያደርጉበት ወደ ቢታንያ ወስዶ እጆቹን ጭኖና ባርኮ እስከ ምትርያርኑት ያለውን ሥልጣን ክህነት ሰጥቶአቸው አርጓል ፥ እነርሱም “ወነበሩ በቤተ መቅደስ ሠልፌ እንዘ ይባርክዎ ወይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር (ዘወትር እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በቤተ መቅደስ ኖሩ) ይላል (ሉቃ. ፳፬ ፣ ፶፬-፶፫) እግዚአብሔር በሚመለክበት ክብሩ በሚወደስበት በስሙ ማደሪያ ወደቤተ መቅደስ (ቤተ ክርስቲያን) ለጸሎት መገስገስና መትጋት ቅዱሳን ሐዋርያት የታደሉትን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ መታደል ነው ። የሐዋ. ፪ ፣ ፩-፴፮ ይመልከቱ ።

ጌታችን ከሐዋርያት ተሰናብቶና መመሪያ ሰጥቶ ወደ ሰማይ ሲያርግ የክብሩ መግለጫ የሆነችው ደመና ከዓይናቸው ሠውራ እንደ ተቀበለችውና እርሱም ዕርገቱን ትኩር ብለው ሲመለከቱ በደስታ በልዕልታና በዝማሬ እያመሰገኑ የዕርገቱን በዓል ለማክበር ከተገኙት አዕላፍ መላእክት ውስጥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት፦ “የገሊላ ሰዎች ሆይ ! ወደ ሰማይ

ወደ ገጽ 33 ዞሯል

በዓለ እርገት

ከገጽ 9 የዞረ

እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው'' (የሐዋ.፩፡፱-፲፩)ይላል

ቅዱሳን ሐዋርያት ከዚያች ዕለት ጀምሮ ጌታን በዓይነ ሥጋ ሳይሆን በዓይነ ኅሊና እየተመለከቱ ሠርቶ ያሳያቸውን በቃሉ ያዘዛቸውን እያሰቡና እያሰላሰሉ ፈለጉን ተከትለው ሩጫቸውን እንደ ፈጸሙ ዜና ገድላቸው ያስረዳል ። ይህንኑ ገድል የሚፈጽሙበትንም ኃይል እንደሚሰጣቸው እንዲህ ሲል ነግሮአቸው ነበር ። ''የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል ፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና ፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል'' (ዮሐ. ፲፮፡፲፫) በማለት ነበር ።

እንግዲህ በዚህ ታሪካዊ ዕለት የምናስተውለው ብዙ ነገር አለ ። ይኸውም እምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የፈጸመው ወይም የደመደመው በዚሁ አሁን በያዝነው የዕርገቱ ድርጊት ነው ። እንደሚታወቀው ሁሉ በእግረ አጋንንት የተጠቀጠቀውን ወይም የተረገጠውን የሰው ዘር ነፃ ለማውጣት ከሰማይ ወርዶ ከዲያብሎስ የግዞት ቤት ከሲኦል ማርኮ ወደ ጥንት መኖሪያው ወደ ገነት ለመመለስ ሦሥት ዓመት ከሦሥት ወር ያስተማረው ትምህርት ያደረጋቸውም ተአምራት በጠቅላላው በዚህ ዓለም ላይ በሥጋ ተገልጾ ያከናወናቸው ድርጊቶች ሁሉ ፍጹምነት ያገኙት በድል አድራጊነት ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ መሆኑን በጥልቅ ተገንዝበን የእርሱን በድል አድራጊነት ወደ ሰማይ ዕርገቱን ፤ እኛም ከምርኮኛነት የተመለስንበት ፤ ድኅነታችን የተረጋገጠበት ዕለት መሆኑን ማሰብና ማሰላሰል ይኖርብናል ።

ዳግመኛም ባለቤቱ ''... ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና...'' (ዮሐ.፲፬፡፪) እንዳለው ፤ ይህችን ጊዜ ያዊቷ ዓለማችን ጥለናት የግድ ወደ ዘለዓለማዊው መኖሪያችን መሄዳችን ስለማይቀር ''ዘበላዕሉ ኅልዩ'' (የላይኛውን አስቡ) እንዲሁም ''እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ፤ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን'' (ፊሊጵ.፫፡፳) የተባለውን ቃል እያሰብን ፈቃደ ሥጋችንን አሸንፈን በድል አድራጊነት ሰማያዊቷን ርስት ለመውረስ ያብቃን ፡-